# የ2006 ዝቅተኛው የሰአት የክፍያ መጠን ሕግ

**D.C. Code §§ 2-220.01 – 2-220.11**

የኮንትራት ወይም የመንግስት እርዳታ ተቀባዮች በዉሉ መሰረት አገልግሎት ለሚሰጡ ተባባሪ ሰራተኞች እና ንዑስ ተቋራጮች አሁን ካለዉ የሰአት ክፍያ ያላነሰ ክፍያ ይከፍላሉ።

**ከጃንዋሪ 1፣ 2023 ጀምሮ እስከ ጁን 30፣ 2023 ድረስ የሰአት የክፍያ መጠን በሰዓት $16.50 ነዉ።**

**ከጁላይ 1, 2023 ጀምሮ የዲስትሪክቱ ዝቅተኛዉ የሰአት ክፍያ ወደ $17.00 ከፍ ይላል።**

**ደመወዝን ለመክፈል የተቀመጠው መስፈርቱ ት የሚመለከተዉ ነው፡-**

- **የ $100,000 መጠን ወይም ከዚያ በላይ የሚያገኙ ኮንትራክተሮች እና ተቀባዮች እንዲሁም ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ተቀባይ ከተቀበሉት ገንዘብ $15,000 ወይም ከዚያ በላይ የሚቀበሉ ሁሉም ንዑስ ተቋራጮች፣ እና**
- **የ $100,000 መጠን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት እርዳታ የሚያገኙ እና ተቀባዩ ከሚቀበለዉ የመንግስት እርዳታ $50,000 ወይም ከዚያ በላይ የሚቀበሉ የነዚህ ተቀባዮች ሁሉም ንዑስ ተቋራጮች፣**

**"ኮንትራት" ማለት በተቀባዩ እና በዲስትሪክቱ አስተዳደር መካከል የሚደረግ የፅሑፍ ስምምነት ነዉ።**
**"የመንግስት እርዳታ" ማለት ከኤጀንሲ፣ ከኮሚሽን፣ ከተወካይ ወይም ከሌላ የዲስትሪክቱ አስተዳደር አካል የገንዘብ ጥቅም የሚያስገኝ የእርዳታ፣ ብድር ወይም የታክስ ጭማሪ ፋይናንስ ነዉ።**
**"ተባባሪ ሰራተኛ" ማለት በቀጥታ ከመንግስት እርዳታ ወይም የዲስትሪክት ኮሎምብያ ሰራተኞችን፣ ማንኛዉም ለመንግስት እርዳታ ወይም ዉል አገልግሎቶችን የሚያከናዉን የተቋራጭ ወይም የንዑስ ተቋራጭ ተቀባይ ሰራተኛን ጨምሮ ከቀጠና ኮሎምብያ አስተዳዳሪ ጋር በተደረገ ዉል መሰረት ካሳ በሚቀበል የተቀጠረ ግለሰብ ነዉ። "ተባባሪ ሰራተኛ" የሚለዉ ቃል ዉሉን ወይም የመንግስትን እርዳታ በተመለከተ ጊዜያዊ ወይም ድንገተኛ አገልግሎቶች የሚያከናዉኑትን ወይም በተቋራጩ፣ በተቀባዩ ወይም በንዑስ ተቋራጭ የተቀጠሩትን አይጨምርም።**

**ተፈፃሚ የሚሆኑ የተወሰኑ ልዩ ነገሮች፡-** 1) በዚህ ሕግ ከሚያስፈልገዉ ደመወዝ በላይ የሆኑ በፌደራል ሕግ የሚፈለጉትን የደመወዝ ዉሳኔዎች የሚመለከቱ ዉሎች ወይም ስምምነቶች፣ 2) ነባር እና የወደፊት የመሰብሰብያ ስምምነቶች፤ የወደፊት ስምምነቶች ሰራተኞች አሁን ካለዉ የኑሮ ደመወዝ ያላነሰ ክፍያ እንዲከፈላቸዉ እስካደረገ ድረስ፣ 3) ቁጥጥር በሚደረግባቸው መገልገያዎች የሚከናወኑ የኤሌክትሪክ፣ የስልክ፣ የዉሃ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ዉሎች፣ 4) በከንቲባዋ የታወጀዉን አስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ወይም ምላሽ ለመስጠት ወዲያዉኑ ለሚያስፈልጉ አገልግሎቶች ዉሎች፣ 5) ሰልጣኙ የሰራተኞችን ቦታ እስካልተካ ድረስ የጉዳይ አስተዳደር እና ለስራ ዝግጁነት አገልግሎቶችን ጨምሮ ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን ለሰልጣኞች አገልግሎት ለሚሰጡ ተቀባዮች የተሰጠ ዉል፣ 6) በትምህርት ቤት የእረፍት ግዜ ዉስጥ የተቀጠሩ ዕድሜያቸዉ ከ22 ዓመት በታች የሆኑ ሰራተኞች ወይም በሳምንት ከ25 ሰዓታት በታች የሚሰሩ የሙሉ ግዜ ተማሪ ሆነዉ የተመዘገቡ፣ 7) በመንግስት እርዳታ የተሰራ ወይም የተሸሻሉ ንብረቶችን የሚይዙ ተከራዮች ወይም የችርቻሮ ተቋማት፤ ቀጥተኛ የዲስትሪክት መንግስት እርዳታ ደረሰኝ እስካልተገኘ ድረስ፣ 8) ከ50 የማይበልጡ ግለሰቦችን የሚቀጥሩ እና ለ 501(c)(3) ደረጃ ብቁ ያልሆኑ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ሰራተኞች፣ 9) የMedicaid አገልግሎት አቅራቢዎች ለMedicaid አቅራቢዎች ቀጥተኛ የእንክብካቤ አገልግሎት ስምምነቶች፤ የቀጥታ እንክብካቤ አገልግሎቱ በቤት እንክብካቤ ኤጀንሲ፣ በማህበረሰብ መኖርያ ተቋም ወይም በቡድን ቤት በኩል የአእምሮ እክል ላለባቸዉ ሰዎች Home Care Licensure Act of 1983; D.C. Official Code § 44-501; እና 10) የጤና አገልግሎቶችን ለመስጠት በሚተዳደሩ የእንክብካቤ ድርጅቶች እና በጤና እንክብካቤ ሴፍትኔት አስተዳደር ወይም በMedicaid እርዳታ አስተዳደር መካከል የተደረጉ ዉሎች ወይም ስምምነቶች መሰረት እስካልተሰጡ ድረስ።

**የቤት ዉስጥ እንክብካቤ የመጨረሻ ህግ፡-** የሰራተኛ መምርያ ለቤት ዉስጥ እንክብካቤ ሰራተኞች እና የአብሮነት አገልግሎት ለሚሰጡ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ጥበቃን አራዝሟል። በዚህ ኢንዱስትሪ ዉስጥ ያሉ አሰሪዎች አሁን ለመዝገብ አያያዝ ድንጋጌዎች ተገዢ ናቸዉ። 29 CFR ክፍል 552 ይመልከቱ።

**እያንዳንዱ ተቀባይ እና የተቀባይ ንዑስ ተቋራጭ በዚህ ማስታወቂያ ለተሸፈነዉ ለእያንዳንዱ ተባባሪ ሰራተኛ መስጠት እንዲሁም ይህንን ማስታወቂያ በስራ ቦታዉ ላይ ግልፅ በሆነ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት። ሁሉም ተቀባይ እና ንዑስ ተቋራጮች ቢያንስ ለ3 ዓመታት ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ህግ መሰረት በመደበኛ የስራ ሂደት ዉስጥ የተፈጠሩ እና የተያዙ የደመወዝ መዝገቦችን መያዝ አለባቸዉ።**

**የይግባኝ ጥያቄ ለማቅረብ፡- የቅጥር አገልግሎቶች መምርያ፣ ቢሮ የደመወዝ ሰዓት፣ 400 Virginia Avenue, SW, 4th Floor, Washington, D.C. 20024 ይጎብኙ፣ ወደ (202) 671-1880 ይደዉሉ ወይም የይግባኝ ጥያቄዎን በኦንላይንdoes.dc.gov ያቅርቡ። ወደ "File a Claim" ትር ይሂዱ።**